# አድሎና መገለልን በተመለከተ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ፖሊሲ

# (የኤች አይ ቪ/ ኤድስ እና ሰብአዊ መብት)

- ✓ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ፖሊሲ አንቀድ 5.6 እንደተጠበቀ ሆኖ
- ✓ ማንም ሰው የኤች.አይ.ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት በሚስጥር የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፤
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ያለበት ማንኛውም ሰው ሥራ የማግኘት፣ የመማር፣ ሥልጠና የማግኘት እንዲሁም ሕዝባዊ የሆኑ አገልግሎት መስጫዎችን ማለትም የምግብና መጠጥ ድርጅቶች፣ የስፖርት ተቋማትና የመሳሰሉትን የመጠቀም መብቱ የተጠበቀ ነው፤
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ያለበት ማንኛውም ሰው የፈለገበት ቦታ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የመኖር መብቱ የተጠበቀ ነው፤
- ✓ የሕግ ገደብ የተጣለባቸው ሰዎች፣ እስረኞች፣ ተቋማዊ የሆኑ ግለሰቦች ማለትም ሠልጣኞች፣ ጐዳና ተዳዳሪዎች፣ የጦር ሠራዊት እና የመሳሰሉት እንደ ማንኛውም የሕብረተሰብ አካል ከኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ጋር የተዛመደ የመገለል ስሜት ሳይኖር፣ የትምህርት ዕድል፣ የደም ምርመራ፣ በተመላላሽና ተኝቶ የመታከም እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

- ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሕጻናት ከማንኛውም አድሎና መገለል ሊጠበቁ ይገባል፤ እንደ ማንኛውም ህጻን መደበኛ ትምህርት የመከታተል እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ማለትም አብሮ መጫወትን፣ መማርን የመገለል ስሜት ሳይኖር የመሳተፍ መብታቸው የተጠበቀ ነው፤
- ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው/ ሰዎች ስለ ችግሩ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ችግሩን የመቆጣጠር ክህሎት እንዲያዳብሩ እንዲሁም ሕብረተሰቡን ከተጠቀሰው ችግር የመከላከል ኃላፊነት እንዲወጡ ይጠበቃል፤
- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን ሆን ብሎ ማስተላለፍ፣ በሕግ ያስጠይቃል፣ ያስቀጣል፤